# ቴዲ አፍሮ ይፈታ!

ከወለላዬ(welelaye2@yahoo.com)

ቴዎድሮስ ካሳሁን ተደናቂው ወጣት፣
ዲሞክራሲ እንዲያብብ እንዲታይ አንድነት፣
አገር እንድታድግ ሠላም እንዲሰፍን፣
ፍቅር እንዲዳብር ሁሉ እኩል እንዲሆን፣
ሮሮ እንዲቋረጥ ጥላቻ እንዲጠፋ፣
ዛሬ ላይ እያለን እንዲታየን ተስፋ፣
ሬት እንደሆነ ፀብና አንባጓሮ፣
’ውነትን አፍርጦ ሐቅን አሳምሮ፣
ኑ!  እንተባበር ይያያዝ እጃችን፣
ይከበር ስላለ ነፃነት መብታችን፣
ፈለጉ እንዲጠፋ ዓላማው እንዲደርቅ፣
ታጭቷል ለመከራ ለእስራት ለጭንቅ።
ልጅህን አስፈታ እንግዲህ ያገር ሰው!
ንዋይና ሀብትህ ቴዎድሮስ ሙሴህ ነው።

http://www.EthiopiaZare.com